QuickNotes ጃኑዋሪ/2018 ቅጽ-2

**የ2017 ዓመታዊ ሪፖርት ስለ ማቅረብ**

***ያለፈውን የትምህርት ዓመት የሥራ ክንውኖችን በመገምገም ዋና ዋና ጉዳዮችን አጉልቶ የሚያሳይ ሪፖርት አሁን በድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።***

የ 2017 ከ MCPS ለማህበረሰብ የሚቀርብ ዓመታዊ ሪፖርት በዚህ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።
http://www.montgomeryschoolsmd.org/annualreport/2017/

ይህ ሪፖርት ያለፈውን የትምህርት ዓመት ክንዋኔዎች የሚገመግም እና ዋና ዋና ጉዳዮችን አጉልቶ የሚያመለክት ነው። ሪፖርቱ የሚያካትተው ስለተማሪ የትምህርት አፈጻጸም/ክትትል ሁኔታ እና ተማሪዎች በኮሌጅ እና በሥራ ዝግጁነት ስኬታማ እንዲሆኑ ከወዲሁ ለማዘጋጅት MCPS የሚጠቀማቸውን ስልቶች እንዲሁም በተጨማሪ ከባለፈው አስተዳደር ወደ አዲሱ የትምህርት ዋና ኃላፊ ጃክ ስሚዝ/Superintendent Jack Smith የሆነውን የሽግግር ሂደት ነው። በ 2016–2017 የትምህርት ዓመት ክለሳና ማሻሻያ የተደረገባቸው የቦርድ ፖሊሲዎች ተጨምረውበት የሪፖርቱ ዲጂታል ኮፒ እንዲሰፋ ተደርጓል። እንዲሁም ከ MCPS ሥልታዊ የሥራ እቅድ/MCPS strategic plan ላይ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠባቸው ነገሮች፣ ባለፈው ዓመት የተጀመሩ ሥራዎች፣ የተማሪን የትምህርት መቅሰም ሁኔታ የሚገልጹ ማረጋገጫዎች መረጃ/ዳታ፣ እና የሚጠበቅ ምላሽ/a returning favorite፡- በ 2016-2017 የትምህርት ዓመት ውስጥ የተከናወኑ ሥራዎችን በወር ከፋፍሎ ለማሳየት፣በሪፖርቱ ላይ ተካተዋል።

[ዓመታዊ ሪፖርቱን ይመልከቱ](http://www.montgomeryschoolsmd.org/annualreport/2017/)

**ለአዲስ የወላጅ አካዳሚ/Parent Academy ትምህርቶች ይመዝገቡ**

የክረምቱ ወቅት በሂደት ላይ ነው። የወላጆች አካዳሚ አውደጥናቶች/ዎርክሾፖች በነፃ የሚሰጡና ስለ ኮምፒውተር አውታረመረብ ደህንነት/cybersafety፣ ስለ ኮሌጅ አስቀድሞ ማቀድ እና መልካም ግንኙነት የመሳሰሉ በርካታ አርእስቶችን/ጉዳዮችን ይሸፍናሉ።

የMCPS የወላጅ አካዴሚ:- ለወላጆችና ለማህበረሰብ አባላት ለልጆቻቸው የትምህርት ስኬት የሚያግዙ መረጃዎች፣ መገልገያዎች፣ መሳርያዎችና ምክሮችን የሚሰጡ ዎርክሾፖችን ለመከታተል እድል ይሰጣሉ።

የ2018 የክረምት ወራት ዎርክሾፖች ጀምሯል። በተለይም ስለኮሌጅ እና የሥራ ዝግጁነት ቅድመ ዝግጅት/ማቀድ፣ ጭንቀት ያለባቸዉን ልጆች የአያያዝ ስልት፣ ስለ ኮምፒውተር አውታረመረብ እና ማህበራዊ አውታረ መረብ ደህንነት/cybersafety፣ ስለ ግላዊ ትምህርት ፕሮግራም ግንዛቤና ግብ ማወቅ፣ እና በርካታ ሌሎችም ጉዳዮች ስለሚነሱ እንዲያመልጥዎት አይፈልጉም።

የወላጅ አካዴሚ ዎርክሾፖች ነፃ ናቸው። የልጆች እንክብካቤና የትርጉም አገልግሎቶች በሁሉም ስብሰባዎች/ክፍለጊዜዎች ይቀርባሉ። ስለ ኮርሶቹ የተሟላ ዝርዝር ወላጅ አካደሚ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል። እዚህ ለመመዝገብ ይችላሉ። https://stultzde.wufoo.com/forms/2018-winter-parent-academy-registration/

**የታወቀ አገልግሎት ላበረከቱ የሽልማት ጥቆማዎች ክፍት ተደርጓል።**

ለህዝባዊ ትምህርት ምሳሌነት ያለው ከፍተኛ/ታዋቂ አገልግሎት አስተዋጽኦ ላደረጉ እውቅና እና ዓመታዊ ሽልማቶችን የመስጠቱ ፕሮግራም ስፖንሰር የሚደረገው በትምህርት ቦርድ አማካኝነት ነው። ማንኛውም ግለሰብ ይሁን ቡድን እስከ ማርች 1 ቀን 5 p.m ድረስ ጥቆማዎችን ለማቅረብ ይችላል/ትችላለች።

የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ በ2017–2018 ህዝባዊ ትምህርት የላቀ አገልግሎት ላበረከቱ ለተሸላሚነት ጥቆማዎችን እየተቀበለ ነው። ሽልማቶቹ በቦርድ ስፖንሰር የተደረጉት ተማሪዎችን፣ ቡድኖችን እና ድርጅቶችን ጨምሮ በህዝባዊ ትምህርት ምሳሌነት ያለው አስተዋጽኦ ላበረከቱ አድናቆትን ለማሳየት ነው።

ጥቆማዎች በሚከተሉት ዘርፎች ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡-

- የማህበረሰብ ግለሰብ
- የማህበረሰብ ቡድን
- ቢዝነስ
- የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች ሠራተኞች
- የት/ቤት አገልግሎት በጎ ፍቃደኛ
- በፈርቀዳጅነት የሚጠቀስ/የምትጠቀስ ግለሰብ

ለ "ፈርቀዳጅ ግለሰብ" ሽልማት የሚጠቀሙ ግለሰቦች አሁን በሥራው ላይ የሚገኙ ባይሆኑም፣ ነገር ግን ባለፉት ጊዜያት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ። የተጠቋሚዎቹ አስተዋጽኦ ለረዥም ጊዜ በትምህርት ሥርዓቱ ላይ አዎንታዊ ተጽኖ ያሳደረ መሆን አለበት።

በሌሎቹ ዘርፎች የሚደረጉ ጥቆማዎች ባለፉት ሦስት ዓመታት ለህዝባዊ የትምህርት ሥርዓት በቁርጠኝነት ያገለገሉ እና የሚደግፉ ግለሰቦችን (የ MCPS ተማሪዎችን ጨምሮ)፣ ቡድን፣ ወይም ድርጅቶች እንደሚከተለው የሚገለጽ፡-

- ለMCPS ፕሮግራሞች የተደረገ ወደርየለሽ የጊዜና የሙያ አስተዋፅኦ
- በተምሳሌነትነት የሚጠቀስ ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት መፍጠር ማሳደግ እና/ወይም ተግባራዊ ማድረግ መቻል፣ ወይም
- አጠቃላይ የትምህርት ሥርዓቱን የሚጠቅም አስተዋጽኦ

የጥቆማ ቅጾቹን በስድስት ቋንቋዎች በትምህርት ቦርድ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል። የጥቆማ ቅጽ በፖስታ እንዲደርስዎ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር፡- 301-279-3617 ይደውሉ።

**ጥቆማ የተጻፈበት ቅጽ ወደ ቦርዱ ጽ/ቤት እስከ ማርች 1 ከ 5 p.m በፊት መድረስ አለበት።** ቅጾቹን ሞልተው በአውታረ-መረብ/online፣በፖስታ ቤት፣ በኢ-ሜይል ወይም በፋክስ ለ Montgomery County Board of Education, 850 Hungerford Dr., Room 123, Rockville, MD, 20850; በፋክስ/fax ቁጥር 301-279-3860, ወይም email ለ Becky Gibson ይላኩ።

የመጠቆሚያ ቅጾች እዚህ ይገኛሉ።

**ፌብሯሪ 28 በሰመር ወቅት ስለሚካሄዱ ትምህርታዊ የመዝናኛ እድሎች (Summer Opportunities Fair) ማስተዋወቂያ ቀን**

በሰመር ወቅት ስለሚዘጋጁ የካምፕ ጉዞዎች፣ ፕሮግራሞች እና የበጎ ፈቃድ እንቅስቃሴዎች የአካባቢ እና የክልላዊ አዘጋጆች/አቅራቢዎች ተገኝተው በትምህርት-እድሜ ክልል የሚገኙ ተማሪዎችን ያነጋግራሉ።

እሮብ፣ ፌብሯሪ 28 በሚካሄደው ዝግጅት ላይ ወላጆች ተገኝተው በትምህርት-እድሜ ለሚገኙ ልጆች ያሉትን በርካታ እድሎች ማሰስ እና የአካባቢ እና ክልላዊ አዘጋጆችን ስለ ሰመር ካምፕ፣ ፕሮግራሞች እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ለማነጋገር እድሉን ለመጠቀም ይችላሉ። በዝግጅቱ ሥፍራ፣ ወላጆች የፕሮግራም ሰራተኞችን ማግኘት፣ ማመልከቻዎችን መውሰድ፣ ስለ ፋይናንስ እርዳታ መረጃዎች ለማግኘት ይችላሉ። በዓሉ ከ7 እስከ 8:30 p.m. በCarver Educational Services Center, 850 Hungerford Drive in Rockville ይካሄዳል።

ለዝግጅቱ ቀን ይመዝገቡ ወይም በስልክ ቁጥር፡- 240-314-4825 ይደውሉ።
http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/parentacademy/

**ተማሪ የትምህርት ቦርድ አባልነት/SMOB እጩዎችን ለማቅረብ ክፍት ነው።**

በ 2018–2019 ተማሪ የቦርድ አባል ሆኖ እንዲያገለግል/እንድታገለግል ማንኛውንም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ለመጠቆም ይቻላል። ጥቆማ ለማቅረብ የተሰጠው የጊዜ ገደብ ሐሙስ፣ ጥር 25 ነው።

የ 2018–2019 የ MCPS ተማሪ የቦርድ አባል በእጩነት ጥቆማ ማቅረቢያ ጊዜ ሐሙስ ጃኑዋሪ 25 እስከ 5 p.m ክፍት ሲሆን፣ማንኛውም በ MCPS ከመካከለኛ ደረጃ እስከ 12ኛ ክፍል ያለ ተማሪ እጩዎችን ለመጠቆም ይችላል/ትችላለች፤ በእጩነት የሚጠቆመው/የምትጠቆመው ተማሪ በዚህ ወቅት ሶፎሞር ወይም ጁኒየር ተማሪ መሆን ይኖርበ(ባ)ታል። የበለጠ ለማወቅ እና እጩ የመጠቆሚያ ቅጽ እዚህ ይገኛል።

**የHBCU ዝግጅት/በዓል ፌብሯሪ 9 ይካሄዳል**

ከተማሪዎች እና ከወላጆች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ እና ኢንፎርሜሽን ለመስጠት በታሪክ የጥቁሮች የነበሩ ኮሌጆች እና ዩንቨርሲቲዎች ከ 60 በላይ ተወካዮች ይገኛሉ።

(Friday, Feb. 9) በታሪክ የጥቁሮች ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች (HBCU) 10ኛ ዓመት ዝግጅት ዓርብ ፌብሯሪ 9 በአልበርት አንስታይን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በከንሲንግተን/Albert Einstein High School, 11135 Newport Mill Road in Kensington ከ 6-8 p.m. ይካሄዳል። ከ 4–7 p.m ቦታው ላይ ከተገኙ መግቢያ ይሰጣል።

ይህ በነፃ የሚካሄድ ዝግጅት ከ 8ኛ–12ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች ከ 60 በላይ በታሪክ የጥቁሮች ኮሌጆች እና ዩንቨርሲቲዎች/HBCUs ተወካዮችን ለማግኘት እድል ይሰጣል። የ HBCU ተወካዮች ብዙ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ያቀርባሉ እናም ለተማሪዎች እና ወላጆች ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ። ዝግጅቱ ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች እና ለወላጆች ስለኮሌጅ ቅድመ-ዝግጅት አውደጥናት/ዎርክሾፕ፣ FAFSA ለመሙላት ዎርክሾፕ፣ ስለስኮላርሽፕ መረጃዎችን/ኢንፎርሜሽን እና በሌሎችም ያተኩራሉ።

በርካታ የ HBCU ተወካዮች ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር በሥፍራው ቃለመጠይቅ ያደርጋሉ። ቃለመጠይቅ/ኢንተርቪው በሚደረግበት ወቅት ተማሪዎች የማመልከቻ/አፕሊኬሽን ክፍያ ሊሰረዝላቸው ይችላል፣ ስኮላርሽፕ የማግኘት እና እዚያው ምደባ የማግኘት እድል ይኖራል።

በድረ-ገጽ ላይ ምዝገባ ማድረግ ያስፈልጋል። እባክዎ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትዎን የኮሌጅ እና ሥራ ኢንፎርሜሽን አስተባባሪ ወይም ካውንስለር ስለ ምዝገባው ያነጋግሩ።

በዚህ ወቅት የነፃ አገልግሎት ለመስጠት ፍላጎት ካለዎት/ፈቃደኛ ከሆኑ Marcia Johnson ን ያግኙ። Marcia_K_Johnson@mcpsmd.org

**የኮሌጅ ፌር ላይ ጊዜአችሁን በውጤታማነት መጠቀም**

ከዝግጅቱ በፊት

- የዝግጅቱን ድረ-ገጽ/fair website ይከታተሉ (ያረጋግጡ) http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/familysupport/hbcu/ እና የት/ቤትዎን ካውንስለር ወይም የኮሌጅ እና ሥራ ኢንፎርሜሽን አስተባባሪ ስለ ምዝገባው ያነጋግሩ።
- የተሳታፊዎችን ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ዝርዝር ተመልከቱና መጀመሪያ የትኞቹ ጋር መሄድ እንደምትፈልጉ እና በቂ ጊዜ ካለችሁ መጎብኘት የምትፈልጓቸውን በቅድሚያ ወስኑ።
- ለመዝጋቢ ሠራተኞቹ የሚያቀርቡትን ጥያቄዎች ዝርዝር ያዘጋጁ።

በዝግጅቱ/በትርኢቱ ወቅት

- በአግባቡ ይልበሱ።
- ካርታ ይኑራችሁ፣ ክፍሉን ቃኙ እና ለጉዞአችሁ የአቅጣጫ ዕቅድ አዘጋጁ። ከከፍተኛ ምርጫዎቻችሁ ውስጥ ቢያንስ የ10ቹን ጠረጴዛዎች ለመጎብኘት ይሞክሩ።
- በሚፈልጉት የኮሌጆች የፖስታ መቀበያ ዝርዝሮች ውስጥ እንድትገኙ ተመዝገቡ።
- ከምትፈልጓቸው ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች መፅሄቶችን አንሱና እንድታነቧቸው ወደቤት ውሰዱ።
- በውይይት ወቅትና የኮሌጅ ተወካዮችን ስታገኙ ማስታወሻ ያዙ።

ዝግጅቱን ስፖንሰር የሚያደርጉት MCPS፣ the Montgomery County Branch of the NAACP እና the Washington Inter Alumni council of the UNCF ናቸው።

**የተማሪ ዝውውር ማመልከቻ ወራት ፌብ. 1 ይጀምራል**

*የዝውውር ሂደቱ የሚጀምረው ወላጆች እና ሞግዚቶች ስለ ት/ቤት ምደባ ዝውውር/ቅያሬ ጠቃሚ መረጃዎች የሚገኝበትን መጽሔት ለማግኘት ከሚችሉበት ከልጁ/ልጅቷ የአካባቢ ት/ቤት ነው።*

ስለልጃቸው ከአካባቢ ት/ቤት ወደ ሌላ ት/ቤት ቅያሬ (COSA) እንዲደረግላቸው የሚፈልጉ ወላጆች ጉዳዮን ፌብሯሪ 1 መጀመር ይኖርባቸዋል። የዝውውሩ ሂደት የሚጀመረው ወላጆች እና ሞግዚቶች ስለ ዝውውር ሂደቱ መግለጫ እና መረጃዎችን እና የዝውውር ቅጽ/COSA form ያለበት መጽሔት ለማግኘት ከሚችሉበት ከአካባቢ ት/ቤት ነው። የCOSA ትንሽ መፅሃፍ በት/ቤቶችና ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።

የኤሌመንታሪ ቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራሞች (የ2ኛ ቋንቋ መማርያ ዘዴ)፣ ወላጆች ዝርዝሮችን ተፈላጊ ፎርሞችን በሁሉም ኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች እና ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ። በ Northeast Consortium (NEC)፣ Downcounty Consortium (DCC)፣ ወይም Middle School Magnet Consortium (MSMC) አካባቢዎች የሚኖሩ ተማሪዎችን ምደባ በሚመለከት፣ በ301-592-2040

Division of Consortia Choice and Application Program Services (ኮንሶርሺያ ምርጫ እና ማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎቶች ክፍል)ን ያግኙ ወይም ድረ-ገጹን ይጎብኙ።

ስለ ሽግግር ሂደት ጥያቄዎች ያላቸው ወላጆች በአካባቢያቸው የሚገኘውን/የምትገኘውን ርእሰመምህር እንዲያገኙ እናበረታታለን። ASK MCPS በስልክ ቁጥር፦ 301-309-MCPS (6277) በመደወል እንግሊዝኛ መናገር የማይችሉ ወላጆችና አሳዳጊዎች የማስተርጎም እርዳታ ለማግኘት ይችላሉ።

የት/ቤት ዝውውሮች